በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ
የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ዩኒቨርሲቲው የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል::

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 (እንደተሻሻለ) ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል:: ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ/የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፤
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፡
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፡
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፡
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፡

<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፤</u>

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በበጀት አመቱ የሂሳብ ማስታወቂያ ላይ በአራት ግለሰቦች ስም በጠቅላላ ድምር ብር 1,491,901.91 በሂሳብ መደብ (4202) (በማነስ) በጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑ፡
2. ክፍያ ከፍለው ቅዳሜ እና እሁድ(Extension) የሚማሩ ተማሪዎችን ላስተማሩ መምህራን የትርፍ ሰአት የተከፈለው ብር 1,054,720.00 ከውስጥ ገቢ መክፈል

ሲገባው ከመደበኛ በጀት የተከፈለ በመሆኑ የመደበኛ በጀት ወጪ ከፍ እንዲልና የውስጥ ገቢ ወጪ ዝቅ እንዲል አድርጎታል።

3. የጋምቤላ ዩኒቨርሰቲ ለአስተዳደር ሰራተኞች ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንን በማስፈቀድ ትርፍ ሰዓት ለሰሩበት በትርፍ ሰዓት የአከፋፈል ስሌት መሰረት መክፈል ሲገባው ለሰራተኛው በምሳ አበል መልክ ብር 450,540.86 እና ከ ብር 400 - 900 ተመን በማውጣት ብር 2,621,160.6 ጠቅላላ በድምሩ ብር 3,071,701.46 ትርፍ ሰአት ለሰሩበት በሚል ሰራተኞቹ ለስራ ጉዳይ ከሚሰሩበት ቦታ ወደ ሌላ ሳይሄዱ አለአግባብ በውሎ አበል ተመን መሰረት ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን በወሩ ውስጥ ምን ያህል ሰዓት እንደሰሩ የማይታወቅና በልዩነት ምን ያህል እንደተከፈለ በኦዲት ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
4. በድምሩ ብር 1,189,610.84 ለተፈጸመው ክፍያ የእጅ በእጅ ሽያጭ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ መቅረብ ሲገባ አላግባብ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የጥሬ ገንዘብ ወጪ የተደረገ በመሆኑ የጥሬ ገንዘብ እና የተከፋይ ሂሳብ ዝቅ እንዲል ያደረገ መሆኑ፣
5. ለጋምቤላ ኮንስትራክሽን ድርጅት የአጥር ግንባታና የጥበቃ ማማ ስራ 3ተኛ ዙር ክፍያ ብር 1,791,230.78፣ እና ለብሔራዊ የጀግኖችና ህጻናት አምባ ብር 200,000.00፣ ጠቅላላ በድምሩ ብር 1,991,230.78 ክፍያ ሲፈጽም ክፍያው በትክክል ለባለ መብቱ ስለመከፈሉና ገንዘቡን ስለመቀበላቸው የሚያሳይ ደረሰኝ ያልቀረበ በመሆኑ አለአግባብ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ዝቅ እንዲል የወጪ ሂሳብ ከፍ እንዲል አድርጎታል፡፡
6. በአጠቃላይ ዩኒቨርስቲው ለየሒሳብ ኮዶቹ ከተፈቀደው በጀት ከመደበኛ በጀት ብር 29,055,040.06 ከካፒታል በጀት ብር 2,364,338.66 ከበጀት በላይ በድምሩ ብር 31,419,378.72 የተጠቀመ መሆኑ፡

ከላይ በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሣ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

1. <u>ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች፤</u>

1.1 በቀን 11/6/2013 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 392001 የክሊኒክ የጤና ባሙያዎች የተረኝነት አበል ብር 44,436.70 ክፍያ የተፈፀመ ሲሆን ስራውን ማከናወናቸው የሰዓት መቆጣጠሪያ አቴንዳንስ ያልቀረበ መሆኑ፣

1.2 ዩኒቨርሲቲው በቀን 02/07/13 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 393302 በሂሳብ መደብ 6313 ለሃዋሳ ዩኒቨርስቲ ሃይድሮሊክ ቤተ ሙከራ ለማቋቋም ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ ብር 1,954,000 ላይ **30%** (ሠላሣ በመቶ) የቅድሚያ ክፍያ ብር 586,200.00 መክፈል ሲገባው **50%** (ሀምሳ በመቶ) ብር 977,000 በመክፈሉ በድምሩ ብር **390,800.00** ከህግና መመሪያ ውጭ የተከፈለ መሆኑ፡

1.3 ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 389,036.05 የተለያዩ መድሃኒትና የህክምና መሳርያዎች ግዥ ሲፈጽም የተገዙት መድሃኒቶችና የህክምና እቃዎች በተገቢው የመድሃኒቶችና የህክምና መሳሪያዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ማለትም ለዚሁ አላማ ተብሎ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የሚታተም የመድሃኒት የገቢ ደረሰኝ ገቢ የማይደረጉ መሆኑ

1.4 የጋምቤላ ዩንቨርሲቲ በቀን 25/08/2013 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 393539 በሂሳብ መደብ 6271 ብር 151,025.00 ለማህበረሰብ ሰላምና ልማት ኮንፈረንስ ስልጠና ኦሪጅናል ሳይቀርብ በኮፒ ማስረጃ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፡

1.5 የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ በ2013 በጀት ዓመት መጠናቀቅ ያለባቸው 12 የግንባታ ስራዎች አፈጻጸማቸው ሲታይ ከ3% እስከ 65.73% አፈፃፀም ያላቸውና በውላቸው መሰረት ግንባታቸውን ያላጠናቀቁ የግንባታ ስራ ተቋራጮች መኖራቸው፡

1.6 በቀን 10/04/13 የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 393962 በሂሳብ መደብ 6324 ለአንድሮኒክስ ኃ/የተ/የግ/ማህ የ1250KV የሁለት ጀኔሬተር ግዥ ብር 25,826,086.00 ከመመሪያው ውጭ ያለውድድር በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ በመሆኑ መንግስት አወዳድሮ ከመግዛት ማግኘት የሚገባውን ጥቅም ያሳጣው መሆኑ፡፡

1.7 ሁለት የስራ ተቋራጮች የቅድሚያ ክፍያ ብር **35,946,766.85** ተሰብሳቢ ሂሳብ ዕዳ ያለባቸው ሲሆን ተመላሽ ሳያደርጉ ስራቸውን ያቋረጡ መሆኑ፣

1.8 በጠቅላላው ብር **83,858,156.34** ከ1 ዓመት እስከ አምስት ዓመት የቆየ ያልተሰበሰበ ሂሳብ መኖሩ፣

1.9 በዩኒቨርሲቲው የሰኔ 30/2013 የሂሳብ ሪፖርት መሠረት ለባለመብቶቹ በወቅቱ ያልተከፈለ ብር **4,660,724.84** ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ፤

1.10 ለየሒሳብ ኮዶቹ ከተፈቀደው በጀት

- ከመደበኛ በጀት ብር 4,141,518.16
- ከካፒታል በጀት ብር 220,302,232.12 ስራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ፡

2. <u>ሌሎች ጉዳዮች፤</u>

2.1 የዩኒቨርሲቲው የንብረት አመዘጋገብ፤ አያያዝ እና አጠባበቅ በፌደራል መንግስት ግዢና ንብረት አስተዳዳር አዋጅ ቁጥር 649/2001 መሰረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- የበጀት ዓመቱ መጨረሻ የቋሚ ንብረት ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፡
- በንብረት መጋዘን ውስጥ ቢን ካርድ፡ የተጠቃሚና ስቶክ ካርድ ያልተቋቋመ መሆኑ፤
- ያለአገልግሎት የተቀመጠ አንድ የዳቦ ማሽን የሚገኝ መሆኑ፣
- አስራ አምስት የሞተር ሳይክሎች ሊብሬና ታርጋ የሌላቸው በንብረት ክፍል ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፣
- 4-8711 ማርቼድስ አውቶቡስ ከአንድ አመት በላይ የቆመና አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፣

2.2. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የዩኒቨርሲቲውን ያለፉትን ዓመታት ሂሳብ ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት መሥሪያ ቤቱ ተገቢውን እርምጃ የወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:-

የ2011 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች

- በድምሩ ብር **5,244,871.89** ለተፈጸመው ክፍያ የእጅ በእጅ ሽያጭ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ መቅረብ ሲገባ አላግባብ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የጥሬ ገንዘብ ወጪ የተደረገ መሆኑ፣

- በድምሩ ብር 4,852,758.70 ለተለያዩ ድርጅቶች ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን ኦሪጅናል ደረሰኝ መያያዝ ሲገባው ኮፒ ደረሰኝ ከወጪ ሰነድ ጋር የተያያዘ መሆኑ

የ2011 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች

- ትምህርታቸውን ለማሻሻል ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለሄዱ መምህራን የበረሃ አበሉ ለማያስፈልጋቸው ቦታዎች በጋምቤላ የአየር ፀባይ ተመን መሰረት ተሰልቶ ያለአግባብ ብር 2,912,403.60 ክፍያ የበረሃ አበል ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- በኃላፊነት ደረጃ ለሌሉ ሠራተኞች /ባለሙያዎች 20% የደመወዝ ANNUALIZATION ብር 157,926.00፤ Position Allowance ብር 69,750.00 እና የሞባይል ካርድ ብር 16,200.00 በድምሩ ብር 243,876.00 አላግባብ ክፍያ መፈፀሙ ፣
- ከዩኒቨርሲቲው በቀረበ ማስረጃ መሰረት በበጀት ዓመቱ የመኖሪያ ቤት ለተሰጣቸው 9 ግለሰቦች የቤት አበል ብር 38,800.00 አላግባብ የተከፈለ መሆኑ
- የዩኒቨርሲቲው መምህራን ለትምህርት ወደ ዉጭ ሀገር ሄደው ለሚማሩ በየወሩ ግማሽ ደመወዝ ብቻ መክፈል ሲገባዉ ሙሉ ደመወዝ በመክፈሉ በልዩነት ለደመወዝ ብር 49,860.00፣ የበረሃ አበል ብር 98,280.00 በድምሩ ብር 148,140.00 ከመመሪያ ዉጪ የተከፈለ ሂሳብ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡
- የባለበጀት መሥሪያ ቤቶች የቦርድ አመራር የቦርድ አበል ክፍያ፡- ለሰብሳቢ ብር 1,300.00፣ ለአባል ብር 1,200.00 እና ለጸሐፊ ብር 525.00 ሆኖ እንዲከፈል፤ የተወሰነ ሲሆን ብር 50,150.00 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
- ለቢሃ የግንባታ ሥራ ተቋራጭ በተዘጋጀው ሶስተኛ የክፍያ ምስክር ወረቀት ከተፈጸመው ብር¬ 13,310,348.15 ክፍያ ውስጥ ለብር 2,034,038.15
- ለኮራኮን ሥራ ተቋራጭ በተዘጋጀው አራተኛ የክፍያ ምስክር ወረቀት ለቀረበው ክፍያ ከተፈጸመው ብር¬ 14,820,548.81 ውስጥ ለብር 3,772,507.20
- ለቢሃ የግንባታ ሥራ ተቋራጭ በተዘጋጀው አምስተኛ የክፍያ ምስክር ወረቀት ለቀረበው ክፍያ የተፈጸመው ከብር¬ 11,627,399.57 ውስጥ ብር 6,743,998.48 በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ መወራረዱ፤

- በኤሌክሮኒክስ ሂሣብ መመዝገቢያ አይቤክስ ላይ ከወትሮ የተለየ በዴቢት ብር 2,521,944.62 በመታየቱ ምክንያት የዓመቱን ሂሣብ ለመዝጋት ባለመቻሉ በማለት በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 71273 በዴቢት 6323 በክሬዲት 4103/001-----ብር 2,521,944.62 ያለምንም ደጋፊ ማስረጃ የሂሳብ ምዝገባ የተከናወነ መሆኑ
- በቀን 09/01/10 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ 277294 ለICT መሰረተ ልማት በማለት ለመንግስት ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ሂሳብ ቁጥር ገቢ እንዲደረግ በታዘዘው መሰረት ብር 51,000,000.00 ያለ ምንም አገልግሎት ወይም ዕቃ ሳይቀርብ እንዲሁም ኤጀንሲው ባንክ ለገባው ሂሣብ ዩኒቨርሲቲው አገልግሎቱን እስከሚያገኝ ድረስ በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው አላግባብ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፣
- ለቤተ ሙከራ ተብሎ የተፈጸመው ክፍያ፤ በድምሩ በብር 275,241.50 ለውኃ አገልግሎት ግዥ፡ ለሽንት ቤት የተመጠጠበት፡ ዶን ቦስኮ ኮሌጅ ለተግባር ት/ት የተከፈለ፡ ለስልክና ለኢንተርኔት በድምሩ ብር 301,473.09፤ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ያልተያያዘ መሆኑ፤ ለተክለብርሃን አምባዬ የግንባታ ሥራ ተቋራጭ አምስተኛ ክፍያ የምስክር ወረቀት ከተፈጸመው ከብር¬ 64,706,530.44 ክፍያ ውስጥ የብር 47,389,622.53 ከተቋራጩ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ያልቀረበለት በመሆኑ፤

በጠቅላላው ብር 47,966,337.12 የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳይቀርብ ሂሳቡ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

- <u>በ2008 በጀት ዓመት፤</u>
- በ2008 በጀት ዓመት ብር 6,934.00 የዩንቨርሲቲው የቢዚነስና ኢኮኖሚክስ ዲን እና የዩንቨርሲቲዉ የግብርና ኮላጅ ዲን የሆኑት ለመምህራን ቅጥር ወደ ህንድ ሀገር የሄደበት አላግባብ በብልጫ የተከፈላቸው መሆኑ፣

ከላይ የተዘረዘሩት ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያሳሰብን ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ አልተወሰደም፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

ታህሳስ 2014 ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ

የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

መግቢያ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርሲቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርሲቲውን የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፣

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡ አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲቱ በዩኒቨርሲቲው የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡ የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ሲሆን የሂሳብ

መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1.<u>የባንክና የሳጥን ሂሳብ</u>፣

1.1 <u>የጥሬ ገንዘብ ሂሳብን በተመለከተ</u>

1.1.1 <u>ግኝት</u>፣

የኢትዮጲያ የፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 970/2008ን ለማስፈፀም በወጣው የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀፅ 68 ጉድለትን ሪፖርት ስለማድረግ በሚለው ንኡስ አንቀፅ 2 ላይ አጠቃላይ የገንዘብ ጉድለት (አስፈላጊ ሲሆን ግምቱን) ማናቸውንም ተመላሽ ሳይጨምር ጉድለት በተፈፀመበት የበጀት አመት ሂሳብ ሪፖርት ወይም ጉድለት በወቅቱ ሳይታወቅ ሲቀር ተግባራዊ ሊሆን በሚችልበት አመት በመንግስት ሂሳብ ሪፖርት ውስጥ ሪፖርት እንደሚደረግ በሚያዘው መሰረት ማከናወን እንዳለበትና የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 አንቀፅ 8 የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች የመንግሥት ገንዘብና ንብረት ለፀደቀው ዓላማና በተፈቀደው መጠን ብቻ ጥቅም ላይ መዋሉንና ለማናቸውም የተሰበሰበ ገቢ ወይም ወጪ የተደረገ ገንዘብ በህግ ወይም በሌላ አኳኋን የተሰጠ ተገቢ ስልጣን መኖሩን በማረጋገጥ ረገድ ኃላፊነት እንዳለባቸውና የፋይናንስ ኃላፊው ክፍያን የመፈፀምና ገንዘብ የመሰብሰብ አሰራር ጨምሮ የመስሪያ ቤቱን የባንክና የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር የመከታተል ኃላፊነት እንዳለበት ያዛል፡፡ በዚህ መሰረት

የ2013 በጀት ዓመት ወ/ሮ ባንግ ዲዲሙ ብር 1,060,057.73፡አቶ ዴንግ ጋች ብር 368,776.24፡ወ/ሮ መንጉት ኬሎ ብር 47,371.54፡ወ/ሮ ትግል ሙሉጌታ ብር 15,696.40 ጠቅላላ በድምሩ ብር 1,491,901.91 በሂሳብ መደብ (4202) (በማነስ) በጥሬ ገንዘብ ጉድለት የተመዘገበ መሆኑ በኦዲት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

1.1.2 ስጋት፣

የዩኒቨርሲቲው የጥሬ ገንዘብ አያያዝ በደንብና መመሪያው መሰረት ተግባራዊ ካልተደረገ የህግ ጥሰትን ከማስከተሉም በላይ የመንግስት ገንዘብ ለብክነትና ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡

1.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ፣

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በልዩነት የታየው ብር በአስቸኳይ ተጣርቶ በጉድለት የታየው ገንዘብ በዩኒቨርስቲው አካውንት ገቢ ተደርጎ የገቢ ደረሰኝ ሊቀረጥለት ይገባል፡፡

1.1.4. የስራ አመራሩ ምላሽ

ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ በጥሬ (ከባንክ) ወደ ካዝና ገቢ ያደረጉት የጥሬ ገንዘብ እና የተለያዩ የተቋሙን ወጪ ክፍያ ፈጽመው በሠነድ ያቀረቡት መካከል የሰነድ ወይም የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የብር 2,609,884.89 በአይቤክስ ላይ በመታየቱ ይህንን ጉዳይ ለመፍታት በተደረገ ወሳኔ ከ2007 እስከ 2009 ዓም በገ/ያዦች የተንቀሳቀሰ ሠነዶች ተለይተው የብር 1,253,789.39 ያልተመዘገበ ሠነድ ተገኝቶ የገንዘብ ሚኒስቴር አስፈቅደን በ2012 በጀት ዓመት ምዝገባ ተደርጓል ፡ ሆኖም ቀሪው በሒሳብ መደብ ኮድ 4202 ላይ ምዝገባ የተደረገ ሲሆን በቀጣይ የተቋሙ የሚወስደው ውሳኔ በሂደት ላይ መሆኑ እናሳውቃለን ፡፡

2 ከውስጥ ገቢ መከፈል ሲገባው ከመደበኛ በጀት የተከፈለ ክፍያን በተመለከተ

2.1.1 ግኝት፣

ክፍያ ከፍለው ቅዳሜ እና እሁድ(Extension) የሚማሩ ተማሪዎችን ላስተማሩ መምህራን የትርፍ ሰአት የተከፈለው ሂሳብ ከተገቢው የክፍያ ምንጭ ከውስጥ ገቢ መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በቀን 18/08/13 የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 393403 በሂሳብ መደብ 6116 የትርፍ ሰዓት ብር 1,054,720.00 ከመደበኛ በጀት ወጪ ሆኖ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

2.1.2 <u>ስጋት፣</u>

ቅዳሜ እና እሁድ (ኤክስቴንሽን ፕሮግራም) ላሰተማሩ መምህራን የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ከመደበኛ በጀት መከፈሉ ለመደበኛ ሥራ ከመንግስት በሚመደበው በጀት ላይ ከፍተኛ ጫና ሊያሳድር ይችላል፡፡

የዩኒቨርሲቲው የበጀት ቁጥጥር ተገቢ እንዳይሆን እና የመንግስትን መመሪያ እንዲጣስም ሊያደርግ ይችላል፡፡

2.1.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ፣</u>

ዩኒቨርሲቲው የራሱ ገቢ ላለው የተከታታይ ትምህርት ክፍያን ከመደበኛ በጀት መፈፀሙ ተገቢ ባለመሆኑ በጠቅላለው ለተፈፀሙ ክፍያዎች የወጪ ማስተካከያ በማድረግ ወደ መደበኛ ሂሳብ ተመላሽ ተደርጎ እና ለሚመለከተው መ/ቤት ፈሰስ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

2.1.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

ምላሽ አልተሰጠም

3.<u>የወጪ ሂሳብ፣</u>

3.1.<u>ደመወዝና ተዛማጅ ክፍያዎች፣</u>

3.1.4. <u>ከመመሪያ ውጪ ለአስተዳደር ሰራተኞች የተከፈለ ክፍያን በተመለከተ</u>

3.1.4.1.<u>ግኝት፣</u>

በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 8 (ሀ) መሠረት የመንግሥት ገንዘብ ለፀደቀው ዓላማና በተፈቀደው መጠን ብቻ ጥቅም ላይ መዋል እንዳለበትና የፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ስራ ስለሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች፣ ስለክፍያው መጠንና ስለማካካሻ ዕረፍት ስለሚሰጥበት ሁኔታ የወጣ መመሪያ ተራ ቁጥር 9 የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ የሂሳብ ስሌት እና አከፋፈል በሚለው ርዕስ ስር አንድ ሰራተኛ በወር የሚያገኘው የወር ደመወዝ ለ30 ቀናት ሲካፈል በአንድ ቀን የሚያገኘውን ደምወዝ፣ በቀን የሚያገኘው ደመወዝ ደግሞ ለ8 ሰዓት ሲካፈል በአንድ ሰዓት የሚከፈለውን ደመወዝ ይሰጣል፡፡ በዚህ መሰረት አንድ ትርፍ ሰዓት ሥራ የሚሰራ

ሰራተኛ ቢያንስ ከመደበኛ ደመወዙ ውጪ በተጨማሪ፡-ከንጋቱ 12፡00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 4፡00 ሰዓት የሚሰራ የትርፍ ሰዓት ሥራ ለመደበኛ ሥራ በሰዓት የሚከፈለው ደመወዝ በ1.25 ተባዝቶ ከምሽቱ 4፡00 ሠዓት እስከ ንጋቱ 12፡00 ሰዓት የሚሰራ የትርፍ ሰዓት ሥራ የሚከፈለው ደመወዝ በ1.50 ተባዝቶ በሳምንት ዕረፍት ቀናት የሚሰራ የትርፍ ሰዓት ሥራ በሰዓት የሚከፈለው ደመወዝ በ2 ተባዝቶ በህዝብ በዓላት ቀናት የሚሰራ የትርፍ ሰዓት ሥራ በሰዓት የሚከፈል ደመወዝ በ2.5 እና ጠቅላላ በወሩ ውስጥ የሰሩበት ሰዓት ተባዝቶ አበሉ እንደሚከፈለውና የሰራተኛውን ደህንነት ጠብቆ የተሟላ የስራ ውጤት ለማግኘት እንዲቻል አንድ ሰራተኛ በወር ውስጥ እጅግ ቢበዛ ከ60 ሰዓት በላይ ትርፍ ስራ ማሰራትም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ የጋምቤላ ዩኒቨርስቲ ለአስተዳደር ሰራተኞች ሲቪል ሰርቪስ ኮምሽንን በማስፈቀድ ትርፍ ሰዓት ለሰሩበት በትርፍ ሰዓት የአከፋፈል ስሌት መክፈል ሲገባ ለሰራተኛው **በምሳ አበል መልክ** ብር **450,540.86** እና የክፍያ **ተመን ሬት** በሌለው ከ ብር 400 -900 ብር 2,621,160.6 ጠቅላላ በድምሩ **3,071,701.46** ለአስተዳደር ሰራተኞች ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ እንዲሁም በወሩ ውስጥ ምን ያህል ሰዓት እንደሰሩ የማይታወቅና በልዩነት ምን ያህል እንደተከፈለ በኦዲት ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ቀን	የባንክ ወጪማስ መከሪያ	የሂሳብ ኮድ	የሰው ብዛት	የክፍያው ምክንያት	የገንዘብ መጠን
1	07/01/13	395073	6231	19	የተመራቂ ተማሪዎችን ክሊራንስ በትርፍ ሰዓታቸው ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ ለሰሩበት የ20 ቀን የምሳ አበል የተከፈለ	47,248.50
2	07/10/13	393666	6231	126	የምግብ ቤት ሰራተኞች የአርበኞች ቀን እና ኢድ አልፈጥር ትርፍ ሰዓት ለሰሩበት ለ82 ሰው የ10 እና ለ44 ሰዎች የ5 ቀን የምሳ አበል የተከፈለ	109,719.89
3	22/1/13	393201	6231	16	የተማሪዎች ምኝታ ቤት ተቆጣጣሪዎቸ ሰራተኞች ለ12 ሰው የ10 ቀን የምሳ አበል እና ለ4 ሰው የ5 ቀን የምሳ አበል የተከፈለ	14,878.52
4	08/10/13	392074	6231	14	ኢዲአልፈጥር በዓል እና የአርበኞች ቀን ለተማሪዎች ቁርስ እና ኮቭድ-19 ፕሮቶኮል በተያዘዉ ለምግብ ቤት	16,126.50

					ሠራተኞች የ10 ቀን የምሳ አበል የተከፈለ	
5	13/09/23	392073	6231	111	የጥምቀትና የአድዋ በዓል የበዓሉ ቀን ለተማሪዎች ቁርስ ምሳ እና ለሰላሳ መጠጦች ላስተናገዱበት የ5 ቀን የምሳ አበል የተከፈለ	60,753.00
6	23/09/13	392072	6231	129	የፋሲካ በዓል የበዓሉ ቀን ለተማሪዎች ቁርስ ምሳ እና ለሰላሳ መጠጦች ላስተናገዱበት የ10 ቀን የምሳ አበል የተከፈለ	138,134.75
7	14/4/13	395528	6231	86	ለ2012 ዓ/ም ለተመራቂ ተማሪዎች መልሶ ቅበላ የተመራቂ ኮሚቴ አስተባባሪዎች ለ20 ሰው የ10 ቀን አበል እና ለ66 ሰው የ5 ቀን የምሳ አበል የተከፈለ	63,679.70
8	12/12/12	393114	6116	88	በተከታታይና ርቀት ትምህርት ለሚማሩት የዊከንድ ተማሪዎችን ለደገፉበት የትርፍ ሰዓት ክፍያ	602,240
9	26/8/13	393405	6116	66	›› ››	393,960.00
10	18/10/13	393416	6116	85	›› ››	605,120.00
11	30/10/13	393418	6116	84	›› ››	606,200.60
12	9/7/13	393401	6116	67	›› ››	413,640.00
					ድምር	**3,071,701.46**

3.1.4.2. ስጋት፣

መመሪያው ከሚፈቅደው ውጭ ክፍያ ማከናወን የመንግስትን ገንዘብ ለብክነት እንዲጋጥ ከማድረጉም በተጨማሪ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

3.1.4.3. የማሻሻያ ሃሳብ፣

ከመመሪያ ውጪ ክፍያዎችን መፈጸም አግባብነት የሌለው በመሆኑ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ችግር እንዳይከሰት ጥንቃቄ በማድረግ ክፍያ መከናወን ይኖርበታል፡፡

3.1.4.4. የስራ አመራሩ ምላሽ

የክፍያ ተመን የሌለው የሚለው በልምድ ልውውጥ በተገኘ ተሞክሮ የተከፈለ ነው፡

በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 8 (ሀ) መሠረት ፡

- ✓ የሂሳብ መደብ ኮድ 6231 የውሎ አበል ተብሎ የተገለጸው ለሌሎች ማለትም ለምሳ አበል፤ ለውሎ ገባ አበል የሚከፈልባቸው ኮድ በመሆኑ ከላይ በዝርዝር የተጠወቀሱት ክፍያቸው በአጠቃላይ ለምሳ አበል የተከፈሉ ክፍያዎች በመሆኑ በድጋሚ ሠነዶቹ ተረጋግጦ ከኦዲት አስተያየት እንዲሰረዝ እንጠይቃለን

3.1.4.5 የኦዲተሩ አስተያየት

የምሳ አበል የሚከፈልበት ሁኔታ ሰራተኛው በስራው ባህርይ ምክንያት ከመደበኛ የስራ ቦታው 10 ኪ.ሜ ርቆ የሚሰራ ሲሆን ተፈፃሚ ይሆናል እንጂ በሪፖርቱ ላይ ከተገለፀው ግኝት ጋር የማይገናኝ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡

3.1.6.የሰዓት መቆጣጠሪያ አቴንዳንስ ሳይኖር የተከናወነ ክፍያን በተመለከተ

3.1.6.1. ግኝት፣

የፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 1 ማንኛውም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት አገልግሎቱ የተሰጠበት ማስረጃ መያያዝ እንዳለበት ይገልፃል፡፡ በዚህ መሰረት እየተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በጋምቤላ ዩኒቨርስቲ በቀን 11/6/2013 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 392001 የክሊኒክ የጤና ባለሙያዎች የተረኝነት አበል ብር 44,436.70 ክፍያ የተፈፀመ ሲሆን ስራውን ማከናወናቸው የሰዓት መቆጣጠሪያ አቴንዳንስ ሳይኖር የተከናወነ ክፍያ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

3.1.7.2. ስጋት፣

ክፍያዎች ያለደጋፊ ማስረጃ የሚወራረዱ ከሆነ ውስን የሆነው የመንግስት ንብረት አላግባብ እንዲባክን ሊያደርግ ይችላል፡፡በተጨማሪም የመንግስትን ደንብና መመሪያ እንዲጣስ ከማድረጉም ባሻገር ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

3.1.7.3. የማሻሻያ ሃሳብ፣

ክፍያዎች ከመፈፀማቸው በፊት ደጋፊ ማስረጃዎች መኖራቸውን በማረጋገጥ ክፍያ ሊከናወን ይገባል፡፡ለወደፊቱም ተመሳሳይ ችግር እንዳይከሰት ክትትል በማድረግ ክፍያዎች ሊከናወኑ ይገባል፡፡

3.1.7.4. የስራ አመራሩ ምላሽ

ምላሽ አልተሰጠም

3.2. የግዢና ክፍያ ሂሳብ

3.2.1. የመድኃኒት የገቢ ደረሰኝ በተመለከተ፤

3.2.1.1.ግኝት፣

የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር 2006 ዓ.ም ባወጣው የፌደራል ሆስፒታሎች የመድሃኒት አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 001/2006 ተራ ቁጥር 6.2 ማንኛውም መድሃኒት ወደ ሆስፒታሉ ገቢ ሲደረግ የመድሃኒቱን የምርት መለያ ቁጥር ፣ የማንነት መግለጫ፣ መጠን ፣ መለኪያ፣ የነጠላ ዋጋ ፣ የውስጥ መለያ ኮድ እና አገልግሎት ዘመኑን በሚገልጽ ለዚሁ አላማ ተብሎ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የሚታተም የመድሃኒት የገቢ ደረሰኝ መሰረት በበጀት ምንጫቸው ተለይቶ መሆን አለበት፡፡ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በቀን 10/06/0/13 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 393797 በሂሳብ መደብ 6214 ብር 255,781.99፤ በቀን 24/10/0/13 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 392342 በሂሳብ መደብ 6214 ብር 133,254.06 ጠቅላላ በድምሩ ብር 389,036.05 የተለያዩ መድሃኒትና የህክምና መሳርያዎች ግዥ ሲፈጽም የተገዙት መድሃኒቶችና የህክምና እቃዎች በተገቢው የገቢ ደረሰኝ ማለትም ለዚሁ አላማ ተብሎ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የሚታተም በመድሃኒት የገቢ ደረሰኝ ገቢ የማይደረጉ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

3.2.1.2. ስጋት፣

ህግና ደንብን ተፈጻሚ አለማድረግ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡ እንዲሁም መንግስት ለውስጥ ቁጥጥርን ለማጠንከር እንዲሁም ንብረቶችን ከብክነት

እንዲከላከሉ ለማድረግ የሚያወጣቸውን ህጎች ተግባራዊ አለማድረግ ንብረትን ለብክነትና ለብልሹ አሰራር እንዲጋለጥ ለያደርግ ይችላል፡፡

3.2.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ፣

ማንኛውም መድሃኒት ወደ ሆስፒታሉ ገቢ ሲደረግ የመድሃኒቱን የምርት መለያ ቁጥር ፣የማንነት መግለጫ ፣ መጠን ፣ መለኪያ፣ የነጠላ ዋጋ ፣ የውስጥ መለያ ኮድ እና አገልግሎት ዘመኑን በሚገልጽ ለዚሁ አላማ ተብሎ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የሚታተም የመድሃኒት የገቢ ደረሰኝ መሰረት በበጀት ምንጫቸው ተለይቶ መሆን አለበት፡፡

3.2.1.4. የስራ አመራሩ ምላሽ

የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስተር 2006 ዓ.ም ባወጣው የፌደራል ሆስፒታሎች የመድሃኒት አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 001/2006 ተራ ቁጥር 6.2 መሠረት የተቋሙ መድሐኒት ግዥ ሥርዓት ከመንግስት የመድሐኒት አቅራቢ ኤጀንሲ ግዥ ቢፈጸምም ነገር ግን የመድሐኒቱ አጠቃቀም ሥርዓት ሪፖርት የወጪ እና የገቢ ሪፖርት አቀራረብ እንዳልተለመደ እና በወጪ ሰነድ ላይ ተያይዞ እንደማያውቅ እየገለጽን የፌዴራል ዋና መ/ቤትም ልምዱን ስላካፈለን ለቀጣይ አሠራር ተግባራዊ የምናደርግ መሆኑን እናሳውቃለን ፡፡

3.2.2. የቅድሚያ ክፍያን በተመለከተ፤

3.2.2.1. ግኝት፣

ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉን የእቃና የአገልግሎት ግዥ በግዥ መመሪያ ክፍል 4 **አንቀጽ 16.26 ንዑስ አንቀጽ 16.26.1** በመንግሥት ግዥ አፈጻጸም በማንኛውም ሁኔታ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ **30%** (ሠላሣ በመቶ) በላይ የቅድሚያ ክፍያ ሊሰጥ አይችልም፡፡ የሚሰጠውም የቅድሚያ ክፍያ መጠንም በተጫራቾች መመሪያ ላይ መገለፅ ይኖርበታል ብሎ በግልጽ ያስቀመጠ ቢሆንም **የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ** በቀን 02/07/13 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 393302 በሂሳብ መደብ 6313 ለሃዋሳ ዩኒቨርስቲ ሃይድሮሊክ ቤተ ሙከራ ለማቋቋም ከጠቅላላው ውል ብር 1,954,000 ላይ **30%** (ሠላሣ በመቶ) ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ የቅድሚያ ክፍያ ብር 586,200.00 መሰጠት ሲገባው ብር 977,000 **50%** (ሀምሳ በመቶ)

በመስጠቱ በድምሩ ብር 390,800.00 ከህግና መመሪያ ውጭ የተከፈለ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

3.2.2.2. ስጋት፣

- ☞ በግዢ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም እንዳያስገኝ፤ ቁጠባን የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እንዳይቻል ያደርጋል፡፡
- ☞ የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ የግዥ አዋጁን እና መመሪያውን ተከትሎ ግዥዎችን ያለመፈጸም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

3.2.2.3. የማሻሻያ ሃሳብ፣

ዩኒቨርሰቲው ለሚፈጽማቸው ግዥዎች የአቅራቢዎች ቅድመ ክፍያ በግዥ አዋጁና መመሪያው መሰረት እንዲፈጸሙ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

3.2.2.4. የስራ አመራሩ ምላሽ

ምላሽ አልተሰጠ

3.2.3 በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የተወራረደ የወጪ ሂሳብን በተመለከተ

3.2.3.1.ግኝት፣

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 9 ስለመንግስት ገንዘብ ክፍያ በተገለጸው ውስጥ ማንኛውም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ስለሚደረጉ ጥንቃቄዎች ተ.ቁ.(7) ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ሂሳብ ሲወራረድ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ዋናው ደረሰኝ መሆን እንዳለበት እንዲሁም በአንቀጽ 14 የመደበኛና የካፒታል ሥራ ማስኬጃ ወጪ ስር እንደተገለጸው ተ.ቁ. 4) ክፍያ ለሚፈጸምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረቡን መረጋገጥ እንዳለበት መመሪያው ያዛል፡፡ በዚህ መሰረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- ዩኒቨርሲቲው ለተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ለተለያዩ አቅራቢዎች (ድርጅቶች) ተከፍሎ በወጪ

ለተመዘገበው ብር 1,189,610.84 የቀረበው ማስረጃ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

በቀን	የአቅራቢው ድርጅት ስም	የዕቃው ዓይነት	የሂሳብ መደብ	የወጪ/ ማቁ	የገንዘብ መጠን
29/8/2013	ከናሽናል ማርኬተርስ ኃ/የ/የግ ማህበር	6000 ፍሬ ማርከር	6212	392,490	179,400
30/10/2013	ሰለሞን ገ/ማርያም	የቶነርና ብሬከር ግዥ	6218	393,759	407,100
17/10/2013	ከማክሰቴክ ትሬዲንግ	የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ	6218	393,677	436,797.60
10/7/2013	አታ ኮምፒውቴክ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ	ፍላሽ	6218	392224	97,599.93
10/9/2013	ፍሊከር ትሬዲንግ	ኡሁ እና ካርቦን	6212	393,455	68,713.31
ድምር					1,189,610.84

3.2.3.2. ስጋት፤

ማናቸውም ክፍያዎች ሲፈጸሙ ተገቢው እና ተመጣጣኝ ደረሰኝ ካልቀረበ ገንዘቡ ለብክነት ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሰብ የሚወራረድ ከሆነ የመንግስት ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡ ድጋሚ ክፍያ ሊጠየቅበት ይችላል፡፡

1.1.1. የማሻሻያ ሃሳብ፤

ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ ለዕቃዎችና ለአገልግሎት ተከፍሎ ሂሳብ ሲወራረድ ዋናው ደረሰኝ ቀርቦ ለክፍያውም ተመጣጣኝ ደረሰኝ ሊቀርብ ይገባል፡፡ በተጨማሪ በዱቤ እና በአታችመንት አላግባብ የተወራረዱ ሂሳቦች ደረሰኞቹ ሊቀርቡ ይገባል፡፡

3.2.3.4. የስራ አመራሩ ምላሽ

ምላሽ አልተሰጠም

3.2.5 <u>ደረሰኝ የሌለው ወጪን በተመለከተ</u>

3.2.5.1. <u>ግኝት</u>፣

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት ስለመንግስት ገንዘብ ክፍያ ተራ ቁጥር 9 አንቀጽ 3 ላይ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች፡-ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ለሂሳብ ማወራረጃ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ኦሪጅናል ደረሰኝ መሆን እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚህም መሰረት **የጋምቤላ** ዩኒቨርሲቲ ክፍያ መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ

- ለጋምቤላ ኮንስትራክሽን ድርጅት የአጥር ግንባታና የጥበቃ ማማ ስራ 3ተኛ ዙር ክፍያ በቀን 21/04/13 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 393997 በሂሳብ መደብ 6323 ብር 1,791,230.78፤
- ለብሔራዊ የጀግኖችና ህጻናት አምባ በቀን 17/09/13 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 393522 በሂሳብ መደብ 6417 ብር 200,000.00፤ ጠቅላላ በድምሩ ብር 1,991,230.78 ክፍያ ሲፈጽም ክፍያው በትክክል ለባለ መብቱ ስለመከፈሉና ገንዘቡን ስለመቀበላቸው የሚያሳይ የገቢ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

3.2.5.2. <u>ስጋት</u>፣

ዩኒቨርሲቲው አስፈላጊዉ የወጪ ማስረጃ ሳይሟላ ክፍያ የሚፈጽም ከሆነ ስለ ክፍያዉ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያዳግታል፡፡ ኦሪጅናል ደረሰኙ በድጋሚ የወጪ ማወራረጃ ሊሆን ይችላል፡፡

3.2.5.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

ዩኒቨርሲቲው ኦሪጅናል የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ከወጪ ሰነድ ጋር ሳይያያዝ ክፍያ የተፈጸመበት ምክንያት አጣርቶ ማስረጃውን በማያያዝ የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም የዚህ አይነት አሰራር እንዳይከሰት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

3.2.5.4. <u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

ለጋምቤላ ኮንስትራክሽን ድርጅት የአጥር ግንባታና የጥበቃ ማማ ስራ 3ተኛ ዙር ክፍያ በቀን 21/04/13 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 393997 በሂሳብ መደብ 6323 ብር 1,791,230.78፤

ለብሔራዊ የጀግኖችና ህጻናት አምባ ድጋፍ ክፍያ በቀን 17/09/13 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 393522 በሂሳብ መደብ 6417 ብር 200,000.00 ጠቅላላ ከላይ ለተጠቀሱት አድራሻቸው ስላላገኘን የጥሪ ደብዳቤ እየተጻፈላቸው መሆኑን እየገለጽን በቀጣይ በግብረ-መልስ አካተን የምናሳውቅ መሆኑን እንገልጻለን ፡፡

3.2.8 <u>በኮፒ የተወራረደ የስልጠና ሂሳብን በተመለከተ</u>

3.2.8.1.<u>ግኝት</u>፣

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ቁጥር 9 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄዎች ንዑስ ቁጥር-7 ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ሂሳብ ሲወራረድ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ኦሪጂናል ደረሰኝና ሰነዶች መቅረብ እንዳለበት መመሪያው ያዛል፡ ይሁን እንጂ የጋምቤላ ዩንቨርሲቲ በቀን 25/08/2013 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 393539 በሂሳብ መደብ 6271 ብር 151,025.00 ለማህበረሰብ ሰላምና ልማት ኮንፈረንስ ለሰለጠኑበት በኮፒ ማስረጃ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

3.2.8.2. <u>ስጋት</u>፣

የክፍያ ማስረጃ ከሌላ ሰነድ ጋር ተያይዞ በድጋሚ ክፍያ ሊፈጸም ይችላል።

3.2.8.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

የክፍያ ማስረጃ ከሌላ ሰነድ ጋር ተያይዞ በድጋሚ ክፍያ ሊፈጸም ስለሚችል ኦርጅናል ማስረጃው ከሚመለከታቸው አካላት ቀርቦ ከወጪ ማስረጃዎች ጋር መያያዝ አለበት ለወደፊቱም ማንኛውም ወጪ መወራረድ ያለበት በኦርጅናል ማስረጃ ሊሆን ይገባል፡፡

3.2.8.4. <u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

የጋምቤላ ዩንቨርስቲ በቀን 25/08/2013 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 393539 በሂሳብ መደብ 6271 ብር 151,025.00 ለማህበረስብ ሰላምና ልማት ኮንፈረንስ ለሰለጠኑበት በኮፒ ማስረጃ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል። በአንድ የደብዳቤ ማዘዣ ለማህበረሰብ ውይይቶች በቀረበው ፕሮፖዛል የተለያዩ ክፍያዎች በመጠያቃቸው የደበኞቹን እርካታ ለማሳካት ቀሪዎቹን ክፍያዎች ፕሮፖዛሉን እና የወጪ ማዘዣ ደብዳቤ ለክፍያ ቀርበዋል በመሆኑም ለቀጣይ የምንማርበት በመሆኑ ከኦዲት አስተያየት እንዲሰረዝ እንጠይቃለን

3.3.<u>የዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ አፈፃፀም፣</u>

3.3.1. <u>ቀጥታ ግዥን በተመለከተ፤</u>

3.3.1.1. <u>ግኝት፤</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 51 (ሀ) ከአንድ አቅራቢ ግዥ ለመፈፀም ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው፣ የምክር ወይም ተፈላጊው ሌላ አገልግሎት የሚገኘው ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ ይጠቅሳል በዚህም መሰረት ኦዲት ሲደረግ፣ የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲው በቀን 10/04/13 የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 393962 በሂሳብ መደብ 6324 ለአንድሮኒክስ ኃ/የተ/የግ/ማህ የ1250KV የሁለት ጀኔሬተር ግዥ ብር 25,826,086 በአዋጁ መሰረት ያለውድድር ግዥው በቀጥታ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

3.2.1.2. <u>ስጋት፣</u>

ዩኒቨርሲቲው ግዥን በግዥ መመሪያው መሰረት የማይፈፅም ከሆነ በአፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማለትም፣ ቁጠባን፣ የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ማስገኘቱን ለማረጋገጥ እንዳይቻል ሊያደርግ ይችላል፡፡ ግልጽ አሰራር እንዳይኖር እና የመንግስት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ/እንዲባክን/ ምክንያት ሊሆንም ይችላል፡፡

3.2.1.3. <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ዩኒቨርሲቲው ለወደፊቱ ግዥዎች ሲፈፅም በግዥ መመሪያው መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡

3.2.1.4. <u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

የባለ 1250 K.V ጀኔሬተር ግዥ ሂደት በሚመለከት የዩነቨርስቲው ማኔጅመንት ኮሚቴ በቁጥር 15433/ጋምዩ-40/012 በቀን 25/04/2012 ዓ/ም ባስተላለፈው ውሳኔ መሰረት ቀደም ሲል ዩኒቨርስቲው በማነጅመንት በማስወሰን አንድ ጀኔረተር መግዛቱን በመግለጽ ሆኖም ዩኒቨርስቲው ከሚኖረው የማስፋፊያ ስራዎች እና ተመላሽ የሚደረግ ገንዘብ ከመጠቀም አንጻር በሚል ምክኒያት ተጨማሪ ሁለት ተመሳሳይ ጀነረተሮች እንዲገዛ ባስተላለፈው ውሳኔ መሰት በመጀመሪያ ዙር ካቀረበው ከአንድሮኒክስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ግዥው ሊፈጸም ችሏል፡፡

3.2.7. <u>የዋጋ ማስተካከያን በተመለከተ፤</u>

3.2.7.1. <u>ግኝት፣</u>

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 አንቀጽ 16.14 ን.አንቀጽ 16.14.2 ፊደል ሐ መሰረት የዋጋ ማስተካከያን በተመለከተ የማዕከላዊ ስታትክስ ኤጀንሲ የዋጋ ኢንዴክስ ወይም ጠቋሚ ዋጋ መረጃ መስጠት መቻሉ ሲረጋገጥ እንደሆነ ቢገለጽም የጋምቤላ ዩኒቨርስቲ ለአስሚር የህትመትና ማስታወቂያ ስራ ኃ/የተ/የማህበር የፕሮሲዲንግ ህትመት ስራ በውስን ጨረታ ተወዳድሮ ብዛት 300 የአንዱ ዋጋ ብር 300 በአጠቃይ 90,000 ውል የገባ ቢሆንም የማዕከላዊ ስታትክስ የዋጋ ማስረጃ ሳይኖር የዩኒቨርስቲው ማኔጂመንት በደብዳቤ ቁጥር 13956/ጋምዩ-16/013 በቀን 22/7/2013 የአንዱ የፕሮዲንግ ህትመት ዋጋ ከብር 300 ወደ ብር 498.33 የዋጋ ማሻሻያ በማደጉ ምክንያት በልዩነት ብር 198.33 በመስጠት በቀን 3/10/2013 በወጪ.ማስመስከሪያ ቁጥር 393603 ብር 171,923.85፤ የዩኒቨርሲቲዉ ማኔጅመንት ኮሚቴ ከመጋቢት 1/2013 ዓ.ም ጀምሮ የአንድ እንጀራ ዋጋ በብር 10.47 እንዲያቀርብ በወሰነዉ መሰረት በቀን 28/08/2013 የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 392298 ለሲሳይ ደጀን የእህል ችርቻሮ ንግድ ድርጅት ብዛት ለ156,040.00 እንጀራ ብር 1,321,658.80 መክፈል ሲገባው ብር 1,633,738.80 በመክፈሉ በልዩነት ብር

312,080.00 የተከፈለ መሆኑ፤በቀን 23/09/2013 የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 393509 ብዛት ለ139,100.00 እንጀራ ብር 1,178,177 መክፈል ሲገባው ብር 1,456,377.00 በመክፈሉ በልዩነት ብር 278,200.0 ጠቅላላ በድምሩ ብር 762,203.85 መከፈሉ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

3.2.7.2. ስጋት፣

በግዢ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም እንዳያስገኝ፣ ቁጠባን የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እንዳይቻል ያደርጋል፡፡ በጀትን በቁጠባ መጠቀም እንዳይቻልና የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ከመቻሉም በላይ የግዥ አዋጁን እና መመሪያውን ተከትሎ ግዥዎችን ያለመፈጸም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

3.2.7.3. የማሻሻያ ሃሳብ፣

ዩኒቨርሰቲው የሚፈጽማቸው ግዥዎች በግዥ አዋጁና መመሪያው መሰረት እንዲፈጸሙ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

3.2.7.4. የስራ አመራሩ ምላሽ

በየዩኒቨርሲቲዉ ማኔጅመንት ውሳኔ መሰረት የዋጋ ማስተካከያ የተደረገ ነው፡፡

3.3. የግንባታ ስራዎች

3.3.1. የግንባታ ስራዎች አፈጻጸማቸውን በተመለከተ፤

3.3.1.1.ግኝት፣

የፌዴራል መንግስት ሰኔ/2002 ባወጣው የግዢ አፈፃፀም መመሪያ ክፍል 3 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ1መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች የተለያዩ ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በስተቀር ከአቀራቢዎች /ከስራ ተቋራጮች/ ጋር የተደረገውን የውል ስምምነቶች በፍጥነት ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ ይኖርባቸዋል ይላል፡፡ይሁን እንጂ የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ በ2013 በጀት ዓመት መጠናቀቅ ያለባቸው የግንባታ ስራዎች አፈጻጸማቸው ሲታይ በውላቸው መሰረት ግንባታቸውን ያላጠናቀቁ የግንባታ ስራ ተቋራጮች መኖራቸው

ተ.ቁ	የሚከናወነው ፕሮጀክት ዓይነት	ፕሮጀክቱን የሚያከናው ነው ድርጅት /ስም/	የተገባ የውል መጠን/ገንዘብ/ +15%	የዓመቱው አፈፃጸም ደረጃ(%)	የተጀመረበት ወርና ዓ/ም	የሚጠናቀ ቅበት ጊዜ
1	የጥበቃ ማማ እና የአጥር ስራ	ክሮዎን ኮንስትራክሽን	9,736,611.33	55.43%	ታኅሣሥ 21/2012 ዓ/ም	ሰኔ 30/2013 ዓ/ም
2	የጥበቃ ማማ እና የአጥር ስራ	ጋምቤላ ኮንስትራክሽን	8,670,546.64	64.55%	ታኅሣሥ 21/2012 ዓ/ም	ሰኔ 30/2013 ዓ/ም
3	የጥበቃ ማማ እና የአጥር ስራ	ኡጁሉ አዴይ ኮንስትራክሽን	9,617,945.03	45.21%	ታኅሣሥ 21/2012 ዓ/ም	ሰኔ 30/2013 ዓ/ም
4	የጥበቃ ማማ እና የአጥር ስራ	ብርሃኑ ዳዎ ኮንስትራክሽን	7,501,358.31	65.73%	ታኅሣሥ 21/2012 ዓ/ም	ሰኔ 30/2013 ዓ/ም
5	የተማሪዎች ልብስ ማጠቢያና ሻዎር ቤት ግንባታ	ደቤት ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግሌ ማህበር	2,253,192.26	8.00%	ማጋቢት 14/2013 ዓ/ም	ሐምሌ 15/2013 ዓ/ም
6	የተማሪዎች ልብስ ማጠቢያና ሻዎር ቤት ግንባታ	ታታ ሀይቅ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግሌ ማህበር	2,021,785.84	5.00%	የካቲት 25/2013 ዓ/ም	ሰኔ 5/2013 ዓ/ም
7	የተማሪዎች ደረቅ ሽንት ቤቶች ግንባታ	ትኖክ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግሌ ማህበር	1,477,717.22	25.00%	የካቲት 22/2013 ዓ/ም	ሰኔ 02/2013 ዓ/ም
8	የተማሪዎች ደረቅ ሽንት ቤቶች ግንባታ	ራዕይ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግሌ ማህበር	1,611,988.98	25.00%	የካቲት 18/2013 ዓ/ም	ግንቦት 28/2013 ዓ/ም
9	የተማሪዎች መዝናኛ ቲቨ አዳራሽ ግንባታ	ፋራፊስ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግሌ ማህበር	3,446,522.37	6.00%	የካቲት 18/2013 ዓ/ም	ሰኔ 09/2013 ዓ/ም
10	አነሰተኛ ጋራጅ ግንባታ	ዲጋ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግሌ ማህበር	1,799,145.42	3.00%	የካቲት 22/2013 ዓ/ም	ሰኔ 13/2013 ዓ/ም
11	የቤት ውስጥ ሙቀት መቆጣጠሪያ(AC) ግንባታ	ቄብ ኢንጀነሪንግ ኃ.የተ.የግሌ ማህበር	15,962,377.2	5.00%	መጋቢት 01/2013 ዓ/ም	ግንቦት 21/2013 ዓ/ም
12	የውሃ መሰመር ዝርጋታ እና የፍሳሽ መሰመር ዝርጋታ ስራ	ጋምቤላ ከተማ ውሃ ስራዎች ድርጅት	6,203,162.96	45.00%	የካቲት 19/2013 ዓ/ም	ሐምሌ 1/2013 ዓ/ም

3.3.1.2.<u>ስጋት</u>፣

የግንባታው የስራ ሂደት በታቀደለት ጊዜ አለመጠናቀቁ ዩኒቨርስቲው ግንባታው በጊዜው ተጠናቆ ስራዎችን ባለመጀመሩ ከግንባታው ጋር ተያይዞ አገልግሎት የሚያገኘው አካል ተጠቃሚ እንዳይሆን ከማድረጉም ባሻገር የግንባታ ዕቃዎች ከዋጋ መጨመር አንፃር መንግስትን ላልተፈለገ ወጪ ሊዳርገው ይችላል፡፡ግንባታዎች በውላቸው መሰረት ባለማለቃቸው በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ችግር ሊፈጥር ይችላል፡፡

3.3.1.3.<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

የግንባታውን የስራ ሂደት ለዩኒቨርስቲው በስምምነቱ መሰረት እንዲያልቅ በታቀደለት የጊዜ ገደብ ኮንትራክተሮች ጨርሰው እንዲያስረክቡ ክትትል ማድረግና በታቀደለት የጊዜ ገደብ እንዳይጠናቀቅ የሚያደርጉትን ቁልፍ ችግሮችን ለይቶ በማውጣት ከበላይ የማኔጅመንት ሀላፊዎች ጋር በመነጋገር መፍትሄ እንዲያገኙ ማድረግና በኮንትራክተሩ ምክንያት በሚጓተቱ የግንባታ ስራዎች ላይ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

3.3.1.4. <u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

ከላይ የተጠቀሱት አስተያየቶች ተገቢ መሆናቸውን እየገልፅኩ በዋነኝነት ከፕሮጀክቶቹ አለመጠናቀቅ ምክንያት የሆኑትን ፤እንደ ወሰን ማስከበር ጋር ከፍተኛ ችግር ቦታው ውሃማ በመሆኑ በክረምት ለመስራት አለመቻሉ ሲሚንቶ ገበያ ላይ አለመኖር በኮንትራክተሮች በኩል የሚታየው ቸልተኝነት አልፎ አልፎ የሚከሰቱ የፀጥታ ችግሮች እና ሌሎች ከዚህ ጋር ተያያዥ የሆኑት ችግሮች በወቅቱ ስራው እንዳይጠናቀቅ ክፍተት የፈጠረ መሆኑን እየገልፅኩ በተቻለ አቅምና በፍጥነት ፕሮጀክቶቹን ለማጠናቀቅ የምንሰራ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

3.4. <u>ዕዳ እያለባቸው ያቋረጡ ኮንትራክተሮች</u> ፤

3.4.1.1.<u>ግኝት</u>፣

የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ በ2013 በጀት ዓመት የመነሻ ሂሳቦችን ዝርዝር ኦዲት በሚደረግበት ጊዜ **በዋና ግቢ** በሂሳብ መደብ 4251 የስራ ተቋራጮች የቅድሚያ ክፍያ ብር 35,946,766.85 ተሰብሳቢ ሂሳብ ዕዳ ያለባቸውና በበጀት ዓመቱ

ምንም የስራ እንቅስቃሴ የሌላቸው መሆኑ በኦዲት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ቀን	የሂሳብ መደብ	ተቀጽላ ሌጀር	የብር መጠን	ስም	የቆይታ ጊዜ
1	01/11/12	4251	003	23,287,363.96	ተክለብርሃን አምባየ ኮንስትራክሽን	አምስት ዓመት
2	01/11/12	4251	005	12,659,402.89	ቢሀ ኮንስትራክሽን	አምስት ዓመት
			ድምር	**35,946,766.85**		

3.4.1.2.<u>ስጋት</u>፣

በቅድሚያ ክፍያ ወጪ የተደረገው ሂሳብ በጊዜ ገደቡ ውስጥ አለመወራረዱ ለሌላ ስራ ሊውል የሚችለውን የመንግስት ገንዘብ በግለሰቦች ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡ ወደ ማይወራረድበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል፡፡

3.4.1.3.<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በበጀት ዓመቱ ምንም የስራ እንቅስቃሴ የሌላቸው ከስራ ተቋራጮች የሚፈለግ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳቦች በወቅቱ እንዲወራረዱ እና መሰብሰብ የሚገባቸው ከሚመለከታቸው አካላት ገቢ እንዲደረጉ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.4.1.4. <u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

ከ2008 ዓም ጀምሮ የተቋሙን የተለያዩ የግንባታ ሥራዎች እየሰሩ ቢቆዩም በውላቸው መሠረት የተቋሙን ግንባታ ለማጠናቀቅ በተለያየ ምክንያት እያቀረቡ ባለማጠናቀቃቸው የቅድመ ክፍያ የተከፈላቸውን ተመላሽ ሳያደርጉ የእገዳ ደብዳቤ ደርሷቸዋል ፡፡ በቀጣይ ተቋሙ የሚወሰደውን ማንኛውም እርምጃ የቅድመ ክፍያውን ያማከለ ውሳኔ የሚወስን መሆኑን እንገልጻለን ፡፡

4.ተሰብሳቢ ሂሳብ፣

4.1.ግኝት፣

የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ "ለ" የስራ ማስኬጃ ቅድሚያ ክፍያ በ7 ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበትና በንዑስ አንቀጽ "መ" ደግሞ ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ መመሪያው ቢያመለክትም ሰኔ 30/2013 በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ላይ ብር 158,121,238.89 የሚታይ ከዚህ ሂሳብ ውስጥ፡-**ከኮንትራክተሮች የቅድመ ክፍያ ውጪ** በጊዜ ገደቡ መወራረድ ሲገባው በድምሩ ብር 83,858,156.34 ያልተወራረደ ሂሳብ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩም

የሂሳብ መደብ	የብር መጠን	ተሰብሳቢ ሂሳቡ የቆይታ ጊዜ			
		ከ1 ወር - 1 ዓመት	ከ1 ዓመት - 5 ዓመት	ከ5-10 ዓመት	የቆይታ ጊዜው ያልተገለፀ
4201	8,392,517.97		ከ 2007-2013 ዓ.ም		
4202	1,491,901.91		ከ 2007-2013 ዓ.ም		
4203	305,977.01		ከ 2008-2013 ዓ.ም		
4210	67,796,498.62		ከ 2010-2013 ዓ.ም		
4211	731,475.40		ከ 2007-2013 ዓ.ም		
4253	74,767.45				ያልተገለጸ
4273	166,543.06		ከ 2009-2013 ዓ.ም		
4274	4,898,474.92		ከ 2008-2013 ዓ.ም		
ድምር	**83,858,156.34**				

4.2.ስጋት፣

ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ ሳይወራረዱ ለረጅም ጊዜ ማቆየት የመንግሥት ገንዘብ በወቅቱ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው ዓመታዊ ሂሳቡን በወቅቱ ዘግቶ ሪፖርት እንዳያቀርብ ተጽዕኖ ሊፈጥር ይችላል፡፡

4.3.የማሻሻያ ሃሳብ፣

- ዩኒቨርሲቲው ተሰብሳቢ ሂሳቡ ከሚመለከታቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች በወቅቱ መሰብሰብ የሚገባቸው እንዲሰበሰቡ፣ ወደ ወጪነት መቀየር ያለበት ሂሳብ በወቅቱ ተፈፃሚ የሚሆንበትን ጠንካራ የውስጥ አሰራር ሊዘረጋ እና ተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት ተፈጥሮ በሂሳብ አያያዝ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳይኖረው ተገቢ ማስረጃ በመያዝ መሰብሰብና ወደ ወጪነት መቀየር የማይችሉትን ደግሞ ለሂሳብ መዝገቡ እርምት እርምጃ በህጉ መሰረት ሊወሰድ የሚገባ እና
- በፋይናንስ መመሪያው መሰረት ለግዥ ወጪ የተደረጉ ቅድመ ክፍያዎች በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ እንዲሁም ለውሎ አበል ክፍያ ወጪ የተደረጉ ቅድሚያ ክፍያዎች ለመስክ ስራ የወጣው ሰራተኛ በተመለሰ በሰባት ቀናት ጊዜ ውስጥ የሚወራረድበትን ሥርዓት እና ለግዥ ሰራተኞች የሚሰጡ ቅድመ ክፍያዎች በቅድሚያ የተሰጠ ክፍያ ሳይወራረድ ተጨማሪ ሰነድ እንዳይሰጥ ጥንቃቄ በማድረግ ተሰብሳቢ ሂሳቦች ሳይወራረዱ ለበርካታ ጊዜ እንዳይቆዩ መደረግ አለበት፡፡

4.4 የስራ አመራሩ ምላሽ

ከሂሳብ መደብ ኮድ 4201 ፤ 4202 ፤4203 ፤ 4210 ፤ 4211 ፤ 4253 ፤ 4273 ፤4274 የብር 83,858,156..34 የተዘረዘሩት 4201 የጥናት ምርምር ፤ የጉዞ … በወቅቱ የማወራረድ ልምድ ባይኖርም ነገር ግን ተቋሙ እየወሰደ ያለው እርምጃ የሠራተኛውን ማንኛውንም ጥቅማጥቅም ወጪ እንዲሆኑ ተደርጓል ፡፡ 4202 ከ 2007 ዓም ጀምሮ በዋና ግ/ያዥ እና በረ/ግ/ያዥ በሰነድ ወይም በጥሬ በካዝና ላይ ያልተገኘ ፤4203 ከ2007 ዓም ጀምሮ በጥሬ በግለሰቦች ላይ የሚታይ ገንዘብ በብዛት የለቀቁ ሠራተኞች ፤ 4210 ላይ የታይ በውሳኔ ሂደት ላይ የሚገኙ እና በ2014 ሥራቸው ሲጠናቀቅ ፤4211 በግዥ ሠራተኞች ላይ ያለው ዕዳ የተማሪዎች አገልግሎት ላይ የሚታዘዙት ክፍያዎች በየሰዓቱ እና በየቀኑ የፍላጎት ጥያቄ ስለሚቀርብ እያንዳንዱን ወጪ ሳያወራርዱ አስቸኳይ ክፍያ ስለሚታዘዝ እስከ መስከረም 2014 ዓ.ም ድረስ እንዲያወራርዱ ትዕዛዝ ይሰጣል ፡፡ 4253 በአሠራር ስህተት ሳይቀነስ የቀረ መስከረም ወራት ላይ የተስተካከለ፡፡ በመሆኑ በ2014 በጀት ዓመት ሲጠናቀቅ ዕዳው ይስረዛል፡፡ 4274 የአቅራቢ ድርጅቶች ሥራቸውን ሲያጠናቀቁ ተመላሽ የሚደረግ ይሆናል ፡፡

4.5 የኦዲተሩ አስተያየት

4253 በአሠራር ስህተት ሳይቀነስ የቀረ መስከረም ወራት ላይ የተስተካከለ በማለት ምላሽ የሰጡ ቢሆንም ስለመስተካከሉ ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

5.ተከፋይ ሂሳብ፣

5.1.ግኝት፣

የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ ሀ ‹‹ማናቸውም ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብ መያዝ እንዳለበት›› እና በንዑስ አንቀጽ ሐ ‹‹መ/ቤቶች ከተለያዩ አካላት ቀንሰው ያስቀሩትን የግብርና ሌሎች ሂሳቦች ለሚመለከተው ግብር አስገቢ አካል ወቅቱን ጠብቀው ማስተላለፍ እንዳለባቸው›› መመሪያው የሚያዝ ቢሆንም፤ ሰኔ 30/2013 በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ላይ ብር **92,282,644.78** የሚታይ ቢሆንም ከዚህ ሂሳብ ውስጥ፡-**ከኮንትራክተሮች የዋስትና ማስያዣ ሂሳብ ውጪ** በሂሳብ መደብ 5004 ብር 650,336.60 ፤በሂሳብ መደብ 5028 ብር 53,083.55 ፤በሂሳብ መደብ 5054 ብር 3,957,304.69 በድምሩ ተከፋይ ሂሳብ **ብር 4,660,724.84** መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩም

የሂሳብ መደብ	የብር መጠን	የተከፋይ ሂሳቡ የቆይታ ጊዜ				
		ከአንድ ወር - አንድ ዓመት	ከአንድ ዓመት - አምስት ዓመት	ከአምስት - አስር ዓመት	ከአስር ዓመት በላይ	እድሜያቸው ን መለየት ያልተቻለ
5004	650,336.60	2013 ዓ.ም				
5028	53,083.55	2013 ዓ.ም				
5054	3,957,304.69	2013 ዓ.ም				
ድምር	**4,660,724.84**					

5.2. ስጋት፣

ተከፋይ ዕዳዎች በወቅቱ ካልተከፈሉ በቆይታ ብዛት ከፍተኛ የዕዳ ክምችት እንዲፈጠር ሊዳርግ ይችላል፡፡ በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው ዓመታዊ ሂሳቡን በወቅቱ ዘግቶ ሪፖርት እንዳያቀርብ ተጽዕኖ ሊፈጥር ይችላል፡፡

5.3. የማሻሻያ ሃሳብ፣

በዩኒቨርሲቲው የዕዳ ክምችት እንዳይኖር ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ እንዲከፈሉ፣ ወደ ሀብት መቀየር ካለበት እንዲቀየር፣ ተገቢ ማስረጃ የሚቀርብ ከሆነ መከፈል ያለበት ሂሳብ እንዲከፈል ካልሆነም ለሂሳብ መዝገቡ የእርምት እርምጃ በህጉ መሰረት ሊወሰድ ይገባል፡፡

5.4 የስራ አመራሩ ምላሽ

በሂሳብ መደብ ኮድ 5004 ብር 650,336.60 ብር በተቋሙ ላይ ዕዳ በሰኔ /2013 ዓ.ም ላይ የተያዘ ሲሆን በተለያየ ምክኒያቶች ለሠራተኞች ሳይከፈል የቀረ ደመወዝ መሆን እንገልጻለን በሂሳብ መደብ ኮድ 5028 ከተለያዩ ሠራተኞች ብር 53,083.55 ከደመወዝ ተቀንሶ ለ3ኛ ወገን የሚከፈል ሲሆን ግለሰቦቹ ወይም ድርጅቶች ቀርበው ባለመውሰዳቸው መሆኑን እንገልጻለን ፡፡በሂሳብ መደብ ኮድ 5054 በሰኔ 30/2013 ዓ.ም ላይ በአካውንት ቁጥር 1000155614807 ብር 3,957,304.69 ላይ ፈሰስ የተደረገ የተለያዩ ድርጅቶች እና ግለሰቦች የአደራ ገንዘብ ሲሆን ከገንዘብ ሚኒስቴር በሓምሌ ወር 2013 ተጠይቆ ተመላሽ የሚደረግ ይሆናል ፡፡

6. በጀት ሂሳብ፣

6.1.ግኝት፣

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመንግስት በጀት ለሚሸፈኑ ወጪዎች የዩኒቨርሲቲው የበጀት አስተዳደርና አጠቃቀም በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል 3 አንቀጽ 12 እና በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 መሠረት መሆኑን በኦዲት ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ ለዩኒቨርሲቲው ተስተካክሎ የተፈቀደው እና ሥራ ላይ የዋለው በጀት ሲነጻጸር፣

የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ በየሂሳብ መደቡ የተፈቀደለት የዓመት የተስተካከለ መደበኛ በጀት በስራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር ከመደበኛ በጀት ከአስር 10% በላይ ስራ ላይ ያልዋለ 4,141,518,16 እና ከካፒታል በጀት ስራ ላይ ያልዋለ 220,302,232.12 በድምሩ ብር 224,443,750.28 ያልተሰራበት በጀት ከ10% የተገኘ መሆኑና ከመደበኛ በጀት ከበጀት በላይ የተጠቀሙበት 31,254,766.42 እና ከካፒታል በጀት ከበጀት በላይ 2,364,338.66 በድምሩ ብር 33,619,105.08 ከበጀት በላይ የተጠቀሙበት መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡ ***ዝርዝሩ በአባሪ 2 ተያይዟል፡፡***

6.2.<u>ስጋት</u>፣

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከፍተኛ ተራፊ በጀት መገኘት በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ሊሰሩ በዕቅድ የተያዙ ስራዎች ለመከናወናቸው አጠራጣሪ የሚያደርገው ከመሆኑም በተጨማሪ በሌሎች መ/ቤት /ተቋማት/ ሊሰራበት የሚችለውን በጀት በዩኒቨርሲቲው ስም ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ አሰራር ነው፡፡በጀት ሳያስፈቅዱ ከበጀት በላይ መጠቀም ህግን ከመጣሱ ባሻገር በዕቅድ ላልተያዘ ክፍያ ተከፍሎ ሊሆን ይችላል፡፡

6.3.<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

የተጠቀሰው ተራፊ በጀት በስራ ላይ ያልዋለበት ምክንያት ጉዳዩ ከሚመለከተው የስራ ክፍል በበቂ ማስረጃ ሊደገፍ ይገባል፡፡ ዩኒቨርሲቲው የተፈቀደለትን በጀት በመንግስት የፋይናንስ አዋጅ መሰረት በስራ ላይ እንዲያውል የተቋሙ ሥራ አመራር በበጀት አጠቃቀም ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

በጀት ሳይፈቀድ ተጨማሪ በጀት ሳይጠየቅ ወይም ዝውውር ሳይደረግ ከበጀት በላይ ወጪ መፈጸም አግባብ ባለመሆኑ አሰራሩ እንዲስተካከል እና የዩኒቨርሲቲው ዕቅድና ክንውን የተጣጣመ እንዲሆን መደረግ ይገባዋል፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

6.4 የስራ አመራሩ ምላሽ

ምላሽ አልተሰጠም

7.የቋሚና አላቂ ንብረት አያያዝ፣ አጠባበቅና አስተዳደር፣

7.1.1.ግኝት፣

የፌደራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ተራ ቁጥር አምስት ፣ስድስት ፣ሰባት ፣አራት የመመሪያው ዓላማ በሚለው ስር ግልጽ፣ዘመናዊ፣ቀልጣፋና ውጤታማ የመንግሰት ንብረት አስተዳደር በማስፈን ፣የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣የመጠቀም ፣የመቆጣጠር እና አገልግሎቱ ሲያበቃ ወይም አገልግሎት ላይ በማይውሉበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ እንዲወገድ ማድረግ አለባቸው ቢያመለክትም የጋምቤላ ዩኒበርስቲ በዚህ መሰረት እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ የንብረት አያያዝና አጠቃቀም ኦዲት ሲደረግ፣

የቋሚ ዕቃዎች

- በንብረት ክፍል ውስጥ ቢን ካርድ፣ዩሲ፣ስቶክ ካርድ የማይጠቀሙ መሆኑ፣
- የቋሚ ዕቃ መጋዘን ጥበት ምክንያት እቃዎቹ በስርዓት ያልተቀመጡ በመሆኑ ለብልሽትና ለጉዳት የተጋለጡ መሆኑ፣
- ስምንት የኮምፒውተር ዩፒየሶች፣አስር ኮምፒውተሮች፣አምስት ቴሌብዥኖች አንድ ፕሮጀክተር ለብዙ ጊዜ መሬት ላይ በመቀመጣቸው ምክንያት በአቧራ የበላሹ መሆናቸው፣
- የሚወገዱ ስምንት የላፕቶብ ቦርሳዎች ያልተወገዱ መሆኑ፣

አላቂ ዕቃዎች

- ቢን ካርድ፣ዩሲ፣ስቶክ ካርድ በንበረት ክፍል ውስጥ የማይጠቀሙ መሆኑ፣
- ያለአገልግሎት የተቀመጠ አንድ የዳቦ ማሽን የሚገኝ መሆኑ፣

- ያለአገልግሎት የተቀመጡ 2007 ገቢ የሆኑ ትንሹ አስር የመኪና ጎማ የሚገኙ መሆኑ፣
- የሚወገዱ ሶስት ፍሪጆች ያልተወገዱ መሆናቸው፣

7.1.2.<u>ስጋት</u>፣

- በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ ዕቃዎች ያለምንም ድጋፍ በወለል ላይ ማስቀመጥ ንብረቱ ቢበላሽ ለሌላ ተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡

እንዲወገዱ ተለይተው በታወቅና በሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ሪፖርት የተደረጉ አሮጌ ንብረቶች ላይ ወቅታዊ እርምጃ አለመውሰድ ንብረቶቹ ለበለጠ ብልሽት እንዲዳረጉና ዋጋ ወደ ማጣት ሊደርሱ ይችላል፡፡የመንግስት ንብረት በማንቀሳቀስ ወይም በመያዝ የተመደቡ ሰራተኞች ሲቀያየሩ ያስረከቡት ከወጪ ቀሪ ማስረከብ በሚገባቸው ልክ ለማስረከባቸው አለመረጋገጥ የጠፋ ወይም የጎደለ ዕቃ ላለመኖሩ ለማረጋገጥ አያስችልም

7.1.3.<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

የተጠቀሱት በንብረት አያያዝና አጠባበቅ ላይ የሚታዩ ግድፈቶች ለመንግስት ንብረት መጥፋትና መጉደል መንገድ የሚከፈቱ አሰራሮች ላይ የሥራ አመራሩ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ይኖራበታል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት በንብረት የአያያዝ፤አጠባበቅ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሠረት እንዲሠራ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች በጥብቅ በማስገንዘብ አፈፃፀሙንም በቅርብ ክትትል ማድረግ ይገባል፡፡

7.1.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

1. የካርዶች ግዢ ተጠይቆ ግዢ ባለመፈፀሙ ምክንያት ስለሆነ ግዢ ተፈፅሞ ወደ ሥራ ለመግባት ጥረት ያደርጋል፡፡

2. ኮምፒዉተርና ቴሌቪዥን በአደራ የተቀመጠ መሆኑ ተረጋግጧል ከአቡራ ላይ እንዲነሳ እየተደረገ ይገኛል፡፡

3. የሚወገዱ የላፕቶፕ ቦርሳዎች አባስቸኳይ ይወገዳሉ

<u>አላቂ ዕቃዎችን በሚመለከት</u>

1. የህትመት ሥራ ስለዘገየ ነዉ ማስተካከያ ይደረጋል፡፡

2. ከኤሌክትሮኒክስ ማቴሪያል ጋር አብሮ እንዲወገድ ሪፖርት እተደረገ ነዉ (ከሚያዚያ
4/08/013 ዓ.ም) በተደረገዉ የንብረት ቆጠራ ዘመቻ ጊዜ የተመዘገበ ነዉ፡፡
3.የተቀመጡ ጎማዎች አዲስ ስለሆኑ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ናቸዉ ተብሎ የታሰበ ነዉ በአጠቃለይ የንብረት አያያዝና አጠቃቀም በሚመለከት ከዚህ በላይ ችግር እንዳለ እናያለን፡፡ስለሆነም ለግቢዉ ሰቶር ለቋሚ፤ለአላቂ ለተመላሽ ዕቃ አልተሰራም እጅግ ጠባብ ሰቶር ነዉ ያለዉ

7.2.1.<u>ግኝት</u>

በፌዴራል መንግስት ተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ዓ/ም ክፍል ሁለት አንቀጽ6 ተራ ቁጥር1 ላይ የመንግስት መስሪያ ቤት በግዥ፣በስጦታ፣በዝውውር ወዘተ ተረክቦ ለሚጠቀምበት ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የተለየ ማህደር በመክፈት በማህደሩ ውስጥ መረጃውን መያዝ እንዳለበት ያዛል፡፡ይሁን እንጂ የጋምቤላ ዩኒበርስቲ በዚህ መሰረት የንብረት አያያዝና አጠቃቀም ኦዲት ሲደረግ

- አስራ አምስት የሞተር ሳይክሎች ሊብሬና ታርጋ የሌላቸው በንብረት ክፍል ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፣
- 4-8711 ማርቼድስ አውቶቡስ ከአንድ አመት በላይ አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፣

7.2.2 <u>ስጋት</u>

በብልሽት ምክንያት የቆመ ተሽከርካሪ ወዲያውኑ አጣርቶ እርምጃ አለመውሰድ የመንግሥት ንብረት ለበለጠ ብልሽትና ለከፍተኛ የጥገና ወጪ ሊጋብዝ ይችላል፡፡ እንዲሁም ኤጀንሲው ተረክቦ ለሚጠቀምበት ተሽከርካሪ በማህደሩ ውስጥ የመኪናውን ሙሉ መረጃ አለመያዝ ወይም ማስረጃው እንዳይያዝ ያደረገውን ምክንያት አለማካተት ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

7.2.3.<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

ለወደፊቱ ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት ርክክብ ሲፈጽም የመኪኖቹ ሙሉ ማስረጃ መኖሩን በማረጋገጥ መረከብ ይኖርበታል፡፡እንዲሁም በብልሽት

ምክንያት ቆመው አገልግሎት የማይሰጡ መኪኖች ተጠግነው ወዲያውኑ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

7.2.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

1.አዲሶቹ ሞተር ሳይክሎች GPS ካልተገጠመላቸው ታርጋ የማይሰጥ በመሆኑ አገልግሎት እንዳይሰጡ የቆሙ ናቸው፡፡ሊብሬና ታርጋ እንዲሟላ በሂደት ላይ እንገኛለን፡፡

2.ባሱ ብዙ ጊዜ ብልሽት እያገጠመዉ እና ብዙ ወጪ እየወጣ በሚል በክልሉ ዉስጥ የጥገና ጋራዥ እጥረት በመኖሩ የቆመ ነዉ፡፡አንዱ ብቸኛ ጋርዥ በክልሉ ያለ ሲሆን በዉስጥ ገብቶ እንዲጠገን ጥረት እየተደረገ ነዉ፡፡

8.<u>ከ2008 ዓ.ም እሰከ 2011 ዓ.ም የህጋዊነት ኦዲት ማስተካከያ ያልተወሰደባቸዉ፣</u>

8.1.<u>ግኝት</u>፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምሰት አንቀጽ 17/3 መሠረት ኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡ የወሰዱትን እርምጃ እና አርምጃ ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፊዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ግን ዩኒቨርሲቲው ከ2008 እስከ 2011 በጀት ዓመት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት ከዚህ በታች በተገለጹ ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት ለተደረገልን መልካም የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1.ባለፉት በጀት ዓመታት ኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሳብ መሠረት እርምጃ የተወሰደባቸውን እና ያልተወሰደባቸውን የሚያሳይ ዝርዝር፤					
ተ.ቁ	የ2011 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች	እርምጃ		የተወሰደው እርምጃ	የኦዲተር አስተያየት
		ተወሰደ	ያልተወሰደ		
		✓	X		
1	ዩኒቨርሲቲው በቀን 28/10/2011 በባንክ ወጪ ማስመስከርያ ቁጥር 394288 በሂሳብ መደብ 6271 ላይ ለHDP ስልጠና ለሰጡት ለአስራ ሶስት(13) አሰልጠኞች ለእያንዳንዳቸው ብር 15,000.00 በድምሩ ብር 195,000.00 የተከፈላቸው ሲሆን የተከፈለ ክፍያ ስልጠናው በትክክል ስለመሰጠቱ ስልጠናው ለማን እንደተሰጠ የሚገልጽ ወይም የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፣	✓			
2	የቦርድ አመራር አበል ክፍያ በመመሪያ መሠረት ስለመከፈሉ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ብር 61,560.00 በብልጫ ተከፍሎ መገኘቱ፣	✓			
3	በድምሩ ብር 5,244,871.89 ለተፈጸመው ክፍያ የእጅ በእጅ ሽያጭ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ መቅረብ ሲገባ አላግባብ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የጥሬ ገንዘብ ወጪ የተደረገ መሆኑ፣		X		

4	በድምሩ ብር 4,852,758.70 ለተለያዩ ድርጅቶች ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን ኦሪጅናል ደረሰኝ መያያዝ ሲገባው ኮፒ ደረሰኝ ከወጪ ሰነድ ጋር የተያያዘ መሆኑ		X		
ተ.ቁ	የ2010 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች	እርምጃ		የተወሰደው እርምጃ	የኦዲተር አስተያየት
		ተወሰደ	ያልተወሰደ		
		✓	X		
1	የውስጥ ገቢን ለማመንጨት የወጣው ወጪ ለአስተዳደር ሠራተኞች ብር 450፣ 400፣ 350 እና 250 per exam/ በማድረግ በድምሩ ብር 1,157,880.00 በቦርድ ሳይፈቀድ ክፍያ መፈፀሙ፤	✓		በ2011 በጀት ዓመት ከመደበኛ በጀት ተመሳሳይ ግኝት አልተገኘም፡፡	
2	በዩኒቨርሲቲው ከመደበኛ ወጪ በጀት መፈጸም ያለበትን ግዥ ብር 932,920.00 ከውስጥ ገቢ ያለአግባብ ክፍያ መፈፀሙ፤	✓		በ2011 ተመሳሳይ ግኝት አልተገኘም፡፡	
	ትምህርታቸውን ለማሻሻል ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለሄዱ መምህራን የበረሃ አበሉ ለማያስፈልጋቸው ቦታዎች በጋምቤላ የአየር ፀባይ ተመን መሰረት ተሰልቶ ያለአግባብ ብር 2,912,403.60 ክፍያ የበረሃ አበል ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡		X	በ2011 ተመሳሳይ ግኝት አልተገኘም፡፡	
3	በኃላፊነት ደረጃ ለሌሉ ሠራተኞች /ባለሙያዎች 20% የደመወዝ ANNUALIZATION ብር 157,926.00፤ Position Allowance ብር 69,750.00 እና የሞባይል ካርድ ብር 16,200.00 በድምሩ ብር 243,876.00 አላግባብ በኃላፊነት ደረጃ ላይ ላልሆኑ ሠራተኞች ክፍያ መፈፀሙ ፤		X		በኦዲት ሪፖርት እንዲካተት ተደርጓል፡፡
4	ከዩኒቨርሲቲው በቀረበ ማስረጃ መሰረት በበጀት ዓመቱ የመኖሪያ ቤት ለተሰጣቸው 9 ግለሰቦች ብር 38,800.00 አላግባብ የተከፈለ የቤት		X		

	አበል ሂሳብ መኖሩ በኦዲቱ ታውቋል፡፡				
5	የዩኒቨርሲቲው መምህራን ለትምህርት ወደ ዉጭ ሀገር ሄደው ለሚማሩ በየወሩ ግማሽ ደመወዝ ብቻ መክፈል ሲገባዉ ሙሉ ደመወዝ በመከፈሉ በልዩነት ለደመወዝ ብር 49,860.00፣ የበረሃ አበል ብር 98,280.00 በድምሩ ብር 148,140.00 ከመመሪያ ዉጪ የተከፈለ ሂሳብ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡		X	በ2011 በጀት ዓመትም ተመሳሳይ ግኝት የተገኘ በመሆኑ የማስተካከያ እርምጃ አልተወሰደም፡፡	በኦዲት ሪፖርት እንዲካተት ተደርጓል፡፡
6	የባለበጀት መሥሪያ ቤቶች የቦርድ አመራር የቦርድ አበል ክፍያ፡- ለሰብሳቢ ብር 1,300.00፣ ለአባል ብር 1,200.00 እና ለጸሐፊ ብር 525.00 ሆኖ እንዲከፈል፤ የተወሰነ ሲሆን በመመሪያ መሠረት መከፈሉ ኦዲት ሲደረግ ብር 50,150.00 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡		X	በ2011 በጀት ዓመትም ተመሳሳይ ግኝት የተገኘ በመሆኑ የማስተካከያ እርምጃ አልተወሰደም፡፡	በኦዲት ሪፖርት እንዲካተት ተደርጓል፡፡
	ለቢሃ የግንባታ ሥራ ተቋራጭ በተዘጋጀው ሶስተኛ የክፍያ ምስክር ወረቀት ከተፈጸመው ብር¬ 13,310,348.15 ክፍያ ውስጥ ለብር 2,034,038.15 ለኮራኮን ሥራ ተቋራጭ በተዘጋጀው አራተኛ የክፍያ ምስክር ወረቀት ለቀረበው ክፍያ ከተፈጸመው ብር¬ 14,820,548.81 ውስጥ ለብር 3,772,507.20 ለቢሃ የግንባታ ሥራ ተቋራጭ በተዘጋጀው አምስተኛ የክፍያ ምስክር ወረቀት ለቀረበው ክፍያ የተፈጸመው ከብር¬ 11,627,399.57 ውስጥ ለብር 6,743,998.48 የተወራረደው በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ መሆኑ፤ በድምሩ ብር 12,550,543.83 በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የተወራረደ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡		X	በ2011 በጀት ዓመትም ተመሳሳይ ግኝት የተገኘ በመሆኑ የማስተካከያ እርምጃ አልተወሰደም፡፡	በኦዲት ሪፖርት እንዲካተት ተደርጓል፡፡

	በኤሌክሮኒክስ ሂሣብ መመዝገቢያ አይቤክስ ላይ ከወትሮ የተለየ በዴቢት ብር 2,521,944.62 በመታየቱ ምክንያት የዓመቱን ሂሣብ ለመዝጋት ባለመቻሉ በማለት በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 71273 በዴቢት 6323 በክሬዲት 4103/001-----ብር 2,521,944.62 ያለምንም ደጋፊ ማስረጃ የሂሳብ ምዝገባ የተከናወነ መሆኑ ፣		X		
	በቀን 09/01/10 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ 277294 ለICT መሰረተ ልማት በማለት ለመንግስት ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ሂሳብ ቁጥር ገቢ እንዲደረግ በታዘዘው መሰረት ብር 51,000,000.00 ያለ ምንም አገልግሎት ወይም ዕቃ ሳይቀርብ እንዲሁም ኤጀንሲው ባንክ ለገባው ሂሣብ ዩኒቨርሲቲው አገልግሎቱን እስከሚያገኝ ድረስ በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው አላግባብ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፣		X		
	ለቤተ ሙከራ ተብሎ የተፈጸመው ክፍያ፤ በድምሩ በብር 275,241.50 ለውኃ አገልግሎት ግዥ፡ ለሽንት ቤት የተመጠጠበት፡ ዶን ቦስኮ ኮሌጅ ለተግባር ት/ት የተከፈለ፡ ለስልክና ለኢንተርኔት በድምሩ ብር 301,473.09፤ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ያልተያያዘ መሆኑ፤ ለተክለብርሃን አምባዬ የግንባታ ሥራ ተቋራጭ አምስተኛ ክፍያ የምስክር ወረቀት ከተፈጸመው ከብር¬ 64,706,530.44 ክፍያ ውስጥ የብር 47,389,622.53 ከተቋራጩ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ /Attachment/ ያልቀረበለት በመሆኑ፤ በጠቅላላው ብር 47,966,337. 12 የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳይቀርብ ሂሳቡ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡		X		

	<u>በ2009 በጀት ዓመት፣</u> በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የብር 2,175,405.11 የጥሬ ገንዘብና የመዝገብ ልዩነት የተገኘ መሆኑ፣		X		
	<u>በ2008 በጀት ዓመት፣</u> በ2008 በጀት ዓመት ብር 6,934.00 የዩንቨርሲቲው የቢዚነስና ኢኮኖሚክስ ዲን እና የዩንቨርሲቲዉ የግብርና ኮላጅ ዲን የሆኑት ለመምህራን ቅጥር ወደ ህንድ ሀገር የሄደበት አላግባብ በብልጫ የተከፈላቸው መሆኑ፣		X		

የ2010 እርምጃ ያልተወሰደበት ግኝት

	ቀን	ቨዉቸር	ተከፋለ	የወጪዉ ምክንያት	የተከፈለዉ የአበል መጠን	መከፈል የነበረበት የአበል መጠን	በልዩነት በብልጫ የተከፈለ የገንዘብ መጠን
1	5/12/10	276527	ዶ/ር ወርቁ ነጋሽ	የቦርድ አባል የተከፈለ	12,000.00	1,200.00	10,800.00
2	5/12/10	276527	ዶ/ር ዘሪሁን ተሬሳ	የቦርድ አባል የተከፈለ	12,000.00	1,200.00	10,800.00
3	5/12/10	276527	ዶ/ር ደሌሳ ቡልቻ	የቦርድ አባል የተከፈለ	12,000.00	1,200.00	10,800.00
4	5/12/10	276527	ክቡር አቶ ሰናይ አኩር	የቦርድ ሰብሳቢ የተከፈለ	17,440.00	1,300.00	16,140.00
5	5/12/10	276527	ወ/ሮ አዳነች አስፋዉ	የቦርድ አባል የተከፈለ	14,220.00	1,200.00	13,020.00
ድምር							**61,560.00**

አባሪ 2 የበጀት አጠቃቀም

የሂሳብ መደብ	የተስተካከለ የዓመት በጀት እስከ ሰኔ 30 /2013	በስራ ላይ የዋለ የዓመት ወጪ እስከ ሰኔ 30 /2013	ያልተጠቀሙበት በጀት	የተጠቀሙበት በጀት በመቶኛ	ከበጀት በላይ የተጠቀሙበት
ካፒታል በጀት					
6111	90,367,494.00	93,074,679.36		-3%	2,707,185.36
6116	1,800,000.00	6,523,403.38		-262%	4,723,403.38
6121	32,586,230.00	40,307,822.28		-24%	7,721,592.28
6131	9,940,427.00	10,572,889.16		-6%	632,462.16
6211	1,331,000.00	790,000.00	541,000.00	41%	-541,000.00
6212	1,798,000.00	1,220,111.72	577,888.28	32%	-577,888.28
6213	1,078,114.00	709,077.63	369,036.37	34%	-369,036.37
6216	21,207,381.00	30,003,466.25		-41%	8,796,085.25
6217	2,735,124.00	2,238,252.55	496,871.45	18%	-496,871.45
6219	583,574.00	498,217.69	85,356.31	15%	-85,356.31
6223	3,600,000.00	2,984,377.71	615,622.29	17%	-615,622.29

6231	9,653,369.00	14,130,906.45		-46%	4,477,537.45
6232	4,140,677.00	3,397,194.36	743,482.64	18%	-743,482.64
6243	289,580.00	184,580.00	105,000.00	36%	-105,000.00
6244	1,046,105.00	1,305,448.55		-25%	259,343.55
6252	1,170,248.00	1,636,848.00		-40%	466,600.00
6253	931,926.00	1,096,721.20		-18%	164,795.20
6254	440,389.00	947,847.59		-115%	507,458.59
6255	107,190.00	85,440.00	21,750.00	20%	-21,750.00
6256	412,000.00	372,730.00	39,270.00	10%	-39,270.00
6257	718,130.00	1,152,123.19		-60%	433,993.19
6258	1,043,026.00	861,786.08	181,239.92	17%	-181,239.92
6259	452,020.00	294,520.00	157,500.00	35%	-157,500.00
6271	4,293,841.00	4,893,625.65		-14%	599,784.65
6313	5,224,608.00	5,496,592.36		-5%	271,984.36
6314	670,000.00	462,499.10	207,500.90	31%	-207,500.90
ድምር	**197,620,453.00**	**225,241,160.26**	**4,141,518.16**		

ካፒታል በጀት					
6115	35,051,000.00	37,415,338.66		-7%	2,364,338.66
6231	850,000.00		850,000.00	100%	(850,000.00)
6251	5,000,000.00	998,486.39	4,001,513.61	80%	(4,001,513.61)
6252	2,975,000.00		2,975,000.00	100%	(2,975,000.00)
6257	12,750,000.00		12,750,000.00	100%	(12,750,000.00)
6258	6,800,000.00		6,800,000.00	100%	(6,800,000.00)
6259	5,100,000.00		5,100,000.00	100%	(5,100,000.00)
6271	170,000.00		170,000.00	100%	(170,000.00)
6311	3,400,000.00		3,400,000.00	100%	(3,400,000.00)
6313	50,845,000.00	42,472,325.74	8,372,674.26	16%	(8,372,674.26)
6314	14,399,000.00	8,131,707.29	6,267,292.71	44%	(6,267,292.71)
6322	132,698,500.00	24,884,151.45	107,814,348.55	81%	(107,814,348.55)
6323	134,250,000.00	105,516,256.56	28,733,743.44	21%	(28,733,743.44)
6324	92,494,000.00	72,226,340.45	20,267,659.55	22%	(20,267,659.55)
6412	6,000,000.00		6,000,000.00	100%	(6,000,000.00)

6416	6,800,000.00		6,800,000.00	100%	(6,800,000.00)
ድምር	509,582,500.00	291,644,606.54	220,302,232.12		2,364,338.60